# <u>በስምህ ልጠራ !</u>

የልጅነት ወዳጅ፣ ጋሜ መቁረጫችን
ያርበኝነት ጥንስስ፣ ያመፅ ሙዳያችን
የዳገት የጫካ፣ የዱር ትውስታችን
በዱር በከተማ፣  ፋኖ አስተማሪያችን
የማሌው ደብተራው፣ ቅኔ ዘራፊያችን
በስምህ ልጠራ ልበል ትዝታችን

ተው ስማኝ ሀገሬ፣ ብለን ያዜምንበት
በቃላት ቱማታ፣ የተጫወትንበት
ከጁንታው፣ ከባንዳው፣ የተጣላንበት
ማሌ ድር አድርተን፣ ዲሞ ያቀለምንበት
በቁርና በርሀብ፣ የተፋተግንበት
ስምህ ከስማችን፣......
ደምህ ከደማችን፣ ቁርኝት አለበት

በስምህን ልጠራ፣.........

እንደ አባት፣ እንደ እናት፣ የተሸሸግንብህ
በስምህ ተጠርተን፣ ምለን ያደግንብህ
ለሊት በጨለማ፣ ዘብ የቆምን ለሥራህ
ቀትር ባአደባባይ፣ የታደን በስምህ
ከሰውና ካውሬ፣ የተናጠቅንብህ
ስምህ ታሪካችን፣ አርማችን ነው ስምህ

የወል ቤታችን ነህ፣ የኪዳን ህያው ቃል
ነበር የምንለው፣ የታሪክ መሰላል
የጽናት ትሩፋት፣ ተሻጋሪ ገድል
የመሠረት አለት፣ ትውፊት ያመጽ ግልገል
ኢትዮጵያዊ ወኔ፣ ያብዮት ክንድ ሾተል
በደም የጨቀየ፣ የተጋድሎ መድብል
የነጻነት ጠኔ፣ ያገር መውደድ ቁስል
የትግል ጉልላት፣ የማእበል ደለል
እንዳምና ካቻምናው፣......
በስምህ ልጠለል፣ ዛሬም አለህ ልበል

በስምህ ልጠራ፣.........

በየቅጥሩ ደጃፍ፣ ስሙን ያስጠራችሁ
በዱር በሸለቆ፣ የተሰደዳችሁ
ግፉንም ችላችሁ በህይወት ያላችሁ
አካል ገብራችሁ፣...........
ቆስላችሁ ደምታች፣ ታሪክ የሰራችሁ
በጽናት ታግላችሁ፣........
ወድቃችሁ፣ ቆማችሁ አርማ ያነሳችሁ
ኢ.ሕ.አ.ፓ ቢሏችሁ፣.........
ኢ..ሕ..አ.ወ.ሊ ቢሏችሁ፣ ኢ.ሕ.አ.ሠ ቢሏችሁ
ስሙ ነው ስማችሁ ገድሉም ታሪካችሁ
የመሰዋእት ልኬት ላገር መቆማችሁ
በድርጅት ፍቅር የመመነናችሁ

ዝናማ ነጭ ኩታ፣ በሂደት ይጎድፋል
ውበትና ለዛም፣ እንደዋዛ ያልፋል
ሎሚ ተራተራ፣ በዘመን ይሰምራል
እኛ ብቻ ደህና፣ ከርሞም ድል ያደርጓናል
ቀን የገበረለ እለት፣ ሃይ ዘራፍ ያሰኛል
ዘራፍ ማለት መልካም ለሁሉም ይበጃል
ትግሉ ከዳር ሳይዘልቅ ቀድሞ ድል ያውጃል
መሆንስ ካልቀረ ፋኖ መሆን ይሻል
አጠፋን ያሉ ለት ስር ሰዶ ያመሻል

በስምህን ልጠራ፣.........

አምባ ገነን ባንዶች ዛሬስ ምን ቀራቸው
ለሀገር ፍቅር ስንል ተረገጥንላቸው
በጥይት ተቆልተን ጭዳ ሆንላቸው
ደማችን አፍስሰን መንበር ገበርናቸው
ለስልጣን ጥማቸው ምንደኛ ሆንናቸው
ተዋርደን ተሰደን ጉልማ ቸርናቸው
በርሀብ ተጨማደን ጥሪት አስያዝናቸው

ዘመን ጉልላቷን ለግፈኞች ሰጥታ
የመከራ ምርጊት ወድቆ በእኛ ፈንታ
አንዴም ሰላም ሳናይ ሳናገኝ እፎይታ
ዓርባ ዓመት በቀንበር ኖረናት ሳንፈታ
እርሻው አረም ውጦት ምርት የለ ከጎታ
ዘሩም ተበትኗል ቀርቷል በየ ቦታ
ቃርሚውን ይሰብሰብ ይቅርብን ሁካታ

ማተቡ  እማይላላ፣ ቢታሰር ቢፈታ
ከአላማው ጋር እሚኖር፣ ህልሙን ያበረታ
ፍጹም ሆኖ እሚዘልቅ፣ ሳይገብር ለቃታ
የሩቅ ምንገደኛ፣ የዛሬው አለኝታ
ደርሷል ወክንዳችን፣ ለሀገር መከታ
የቁርጥ ቀን ልጅ ወግ፣ የማያመነታ

ከተማውን ዳስሶ፣ ገጠሩን አማክሎ
ዱር ገደሉን ጥሶ፣ ሸለቆውን ዘሎ
አለት ተንተርሶ፣ ካፈር ተመሳስሎ
የደም ላብ አፍስሶ፣ ካፈር ተቀላቅሎ
ዱር ለብሶ፣ ሳር መስሎ፣........
ሲረግጡት ስር ሰዶ፣ ሲነቅሉት ጎነቁሎ
ኢ.ሕ.አ.ፓ  ሰርዶ ነው የማይጠፋ በቅሎ

አክሊሉ ህይሉ

(ፍራንክፈርት፣ አክቶበር - 2011)